# ሺህ ዝንብ ቢሰበሰብ
# መግላሊት አይከፍትም!

### ሕብረት ለምን? እንዴትና ከማን ጋር? የሚለውን ለመፈተሽና
### በቅርቡ ስለተቋቋመው የኢትዮጵያ ሁሉን አቀፍ ሀገራዊ የመግባባት ኮሚቴ
### ያለኝን አስተያየት ለማቅረብ ስሚ ከተገኘ።

---

አቶ ሰውየው በሀገሩ
(ዘብሔረ-ኢትዮጵያ ከሰሜን አሜሪካ)

የዚህ ጽሑፍ መነሻ ሕብረት ለምን? እንዴትና ከማን ጋር? የሚለውን ለመፈተሽና በቅርቡ በሰሜን አሜሪካ ሲያትል ከተማ ስለተቋቋመው የኢትዮጵያ ሁሉን አቀፍ ሀገራዊ የመግባባት ኮሚቴ ያለኝን አስተያየት ለማቅረብ ነው። በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ እንዳበደች ውሻ በመካከላችን እየተክለፈለፉ ሕብረተ-ሰቡን ግራ በማጋባት የትግሉን አቅጣጫ ለማሳት የሚወራጩ ብዙ ተዋናዮች በመካከላችን ለመሆነቻው ረጋ ብሎ ላስተዋለ ዕውነታውን በሰኮንድ ሊያየው ይችላል። አብዛኛዎቻችን የመናገር የመጻፍና የመደራጀት መብት ባለበት ዓለም ተቀምጠን፣ ወይ በይሉንታ ተጠምደን፤ አለያ ደግሞ በፍራቻ፣ በጓደኝነት፣ ያገር ልጅነት፣ የመንደር አብሮ አደግነት፣ አምቻና ጋብቻ፤ የግል ጥቅም የምናሳድድ ሆዳሞች ስለሆንና በመሳሰሉት ምክንያት ራሳችንን ተብትበን ሊያስተባብሩን የሚገቡ፤ ለሀገራችን ሕዝብ ሰቆቃም በአንድ ልንቆም ሲገባን በየማግሥቱ በሚፈለፈሉ ተቃዋሚ ድርጅት ነን ባዮች በመካከላችን አለመተማመን እንዲሰፍን አድርገን ካለ ጥያቄ ከሚመስሉን ጋር ስንጓተት ይታያል። ተጠያቂነት በሌለበት ሕብረተሰብ ውስጥ ደግሞ ሁሉም ፖለቲከኛ ሆኖ ብቅ ይላል። ስለሆነም ወያኔ ወደ ሥልጣን ከሚገሠግሥበት ጊዜ አንስቶ አያሌ ሕብረቶች ተመስርተው አንዳንዶቹ ለተወሰነ ጊዜ ተንቀሳቅሰው ሲበተኑ ብዙ አይተናል። ለምንድር ነው ይሄ የሚሆነው ብለን ጠይቀን መልስ ሳናገኝ ወያኔ ውጥረት ውስጥ ሲገባ ከየጎሬው ወጥቶ ሁሉም ሕብረት ሕብረት ሊለን ይሞክራል። በቅርቡ በሲያትል የተደረገው የጥድፊያ ሕብረት ሙከራም ከዚህ ለይቼ አላየውም። ለምን ብትሉኝ በትንሹ ከላይ እንዳነሳሁት በሕብረት ተሰባስበን መሥራት ያቃተን ለምንድር ነው ለሚለውና ሕብረት ለምን? እንዴትና ከማን ጋር? ለሚሉት ጥያቄ ምላሽ ሊሰጡ የሚችሉ ስብስቦች ስላልሆኑ ነው መልሴ።

የአሚሪካን የስለላ ድርጅት ሲ.አይ.ኤ. በዓለም ዙሪያ የሚመለምላቸው ነገር አቀባዮችን "አሴትስ (Assets)" ይላቸዋል። በአማርኛ ቀጥታ ትርጉሙ ዕቃዎች ማለት ነው።ይታያችሁ በድርጅቱ ውስጥ ያሉትን ሰላዮች ሳይሆን የሚመለምሏቸውን ነው።ታዲያ በሀገራችን የፖለቲካ ምህዳር ውስጥ በየማግሥቱ የሚፈለፈሉ ድርጅቶች የማን ዕቃዎች ይሆኑ? የምዕራባውያን? የወያኔ? የሻቢያና የጎረቤት ሀገሮችን አጀንዳ የሚያሽከረክሩ? ኢትዮጵያዊነትን የሚጠሉ እንደ ኦነግ ዓይነት እንቅስቃሴዎች? በሚያስጠይቅ ደረጃ ከሚያደርጓቸው ተግባራት በመነሳት ብጠይቅ አትፍረዱብኝ። እስኪ ተመልከቱት ለአማራ ሕዝብ መብት ለመሟገት ስንት የማራ ድርጅቶች እንደተኮለኮሉ? ለኦሮሞም እንዲሁ? ሕብረ-ብሔራዊ ድርጅቶችም የፖለቲካ ፕሮግራምና ርዕዮት ሳያለያያቸው ባገር ውስጥም ሆነ በውጪ የሚርመሰመሱትን ድርጅቶ

ተመልከቱ። እንዲያውም ከናካቴው የኢሕአፓን ስም በመጠቀም የኢሕአፓ-አንድነት ብሎ የሚንቀሳቀስ የአንጃኞች ቡድንም አለ። ለምን? ብላችሁ ጠይቃችሁ ታውቃላችሁ? ሀገር ወዳዱ የሚከፋፈልበትን ሁሉ እያዘጋጁ በነሱ ብሶ ሲያሾፉብን "የኢትዮጵያ ሕዝብ ተባበሩ ወይም ተሰባበሩ" ብሎናል ይሉናል። "የኢትዮጵያ ሁሉን አቀፍ ሀገራዊ የመግባባት ኮሚቴ" ተብዬውም በመግለጫው ይሄንኑ ነው ያለን። ጉድ እኮ ነው! በኔ በኩል እነዚህን ቡከኖች ያመነ ጉም የዘገነ ብዬአቸዋለሁ።

እስኪ አስቡት ሸንጎ የሚባለው ስብስብ የድርጅቶች ሕብረት ነው ከተባለ ሌላ ሕብረት ውስጥ መቀላቀል ለምን አስፈለገው? ግንቦት ሰባት የሚባለውም እኮ በየጊዜው በአብዛኛው ከጸረ-ኢትዮጵያ ድርጅቶች ጋር ተዋሃድን፣ ሕብረት ፈጠርን የመሳሰሉትን ሲሰብከን፤ የእንቧይ ካብ ሲክብልን የሰነበተ ነው። የአማራ ድርጅቶችም ሕብረት ሊፈጥሩ ነው ሰምቻለሁ። የፖለቲካ ድርጅት ነን ባዮችን መፈልፈሉ አልበቃ ብሎን ሕብረቶችን ልናባዛ ተሽጋገርን ማለት ነው። ታዲያ ይሄ ለጤንነት ነው? መቼ ነው አገር ወዳዶች ይሄንን ዕብደት የምናስቆመው? እስኪ አስቡት ከኢሕአፓ ውስጥ በፕሮግራም ወይም በርዕዮት ተለያይተናል ሳይሆን ግለሰቦችን ኮንነው የአብዛኛውን ድምጽ ረግጠው የወጡ ሰዎች ኢሕአፓዎች ነበርንና የኢሕአፓ ስም ይገባናል ዓይነት ኢሕአፓ-አንድነት ብለው ሲንቀሳቀሱና የተለያዩ ድርጅቶችም እንፈጥረዋለን ከሚሉት ሕብረት ውስጥ እንዲሳተፉ ሲፈቅዱላቸው ለሕዝቡ ምን እያሉት ነው? ንቀት ወይስ ትዕቢት? ዕውነት ሕብረትንና የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በሀገራችን ሊያመጡ የሚችሉ ሶዎች የተሰባሰቡበት ናቸው ብላችሁ ታምናላችሁ? ወይንስ ዕቃዎች ናቸው? ተጠያቂነት የሌለበት፣ የተጻፈም ያልተጻፈም የትግል ህግጋት ወይም ስነ-ሥርዓትና ሥነ-ምግባር የማይጠየቁበት ስለሆነ ለወያኔም በከፈቱት ቀዳዳ እየገባ ውዥንብር ሊፈጥር የሚችልበትን ሁናቴ ያመቻቹበትን አሠራር ነው የምታዘበው። ስለሆነም ሀገር ወዳድና ዕውነተኛ ድርጅቶች በጫጫታዎች ተውጠው መልክ ያለው ትግል ለማካሄድ የተቸገሩበትን አያለሁ። ላለፉት 27 ዓመታት ይህ ሁናቴ የተመቸው ለወያኔ ብቻ ነው።

ሸንጎ የሚባለውን ስብስብ ዕውቅና የማልሰጠውም በትንሹ የኢሕአፓን ስም ይዞ የሚንቀሳቀሰውን አጭበርባሪ ቡድን ይዞ እየተንቀሳቀሰ ስለሆነ ነው። በቅርቡም በሲያትል ተመሥረትኩ ያለውም "የኢትዮጵያ ሁሉን አቀፍ ሀገራዊ የመግባባት ኮሚቴ" ይህንኑ ስብስብ አቅፎ ሕብረት ብሎ ብቅ ማለቱ በውስጡ የተካተቱን በሙሉ በጥያቄ ውስጥ እንዳስገባ አድርጎኛል። (ለነገሩማ ይህን የመግባባት ኮሚቴ እንዲቋቋም ጥሪ ያደረገው ኢትዮጵያ ማህበረሰባዊ ድርጅቶች ትብብር ነን የሚሉን 24 የሚሆኑ ማህበረሰባዊ ድርጅቶች የተባሉት አብዛኛዎቹን ብናጤን ለሕብረተ-ሰባችን ካበረከቱት አንጻር ማለቴ ነው አብዛኛዎቹ ቀፎ ድርጅቶች ለመሆናቸው ጥር ጥር የለውም።) ቢከፍቷቸው ተልባ ብቻ!

የኢሕአፓ-አንድነት የሚባለው ቡድን ከኢሕአፓ ተገንጥሎ የወጣበት ምክንያት በግለሰቦች ምክንያት ሳይሆን ለወያኔ አፊዳፊት ፈርመን በሕቡዕ የሚንቀሳቀሰው ኢሕአፓ ይፋ ሆኖ እጁን ለወያኔ ሰጥቶ ተለጣፊ የሚያደርግ አጣብቂኝ ውስጥ የሚያስገባ ክርክር በድርጅቱ ውስጥ አስነስተው ግር ግር በመፍጠራቸውና የድርጅቱ አባላት እንዲወስኑበት በመጠየቃቸው ጉዳዩ ወደ አባላቱ ወርዶ ሀሳቡ በድምጽ ብልጫ ስለወደቀባቸው እንደሆነ ይታወቃል። በዚህም ምክንያት እነ ዶ/ር ጌታቸው በጋሻውና መርሻ ዮሴፍ ሌሎችም የአመራር አባላት የነበሩ ጥቂት አባላትን ይዘው ድርጅቱን ለቀው አኩርፈው ወጥተዋል። ወጥተውም እርስ በርሳቸው ኢሕአፓ ያላስተማራቸውን በዘር ብትንትናቸው ወጥቷል። ዶ/ር ጌታቸው ይባስ ብሎ የኦሮሞ ሕዝብ ኦነግን ከዳር እስከዳር ይደግፋል ብሎ ሲያላዝንብን ለሰማን አዬ ይሄን ወገናችንን ጠበል የሚያደርሰው ዘመድ ጠፋ ብለን እንድንጠይቅም አድርጎን ነበር። ታዲያ ያንን አቋሙን

መቀየሩን አልሰማሁም። ዛሬ የኦሮሞ ወጣት ኢትዮጵያዊነቱን ነው ያረጋገጠውና እንዴት ነው ያንን አቋሙን ሊያጣጥም የሚችለው?። በሰሜን፣ በደቡብ፣ በምሥራቅና በምዕራብ ኢትዮጵያ አመጹን አያፋፋሙ ያሉ ወገኖቻችን ኢትዮጵያዊነትንና አብሮነት ስላረጋገጡልን ማለት ነው። ስለሆነም ነው ወያኔ ተደናግጦ አዲሱን ጠቅላይ ሚኒስቴር ኢትዮጵያዊነት ቀለም የሚቀባው።ኢትዮጵያዊነትን መሠረት ያደረገው ሕዝባዊ አመጽ አስገድዶ ሁሉን ኢትዮጵያችን! ኢትዮጵያችን! እያዘመረ ነው። የሕዝቡን የአመጹ እንቅስቃሴ ላስተዋለ ኢሕአፓ ያሰተማረውን በሥራ ላይ የሚያውልም ይመስላል። ትግሉ ከዘር ክልል ወጥቶ ኢትዮጵያዊነት (አሕጉራዊ) መልክ እንዲዪዝ ስለማድረግግና የሙት ከተማ አድማን ሕዝቡ እንዴትና ለምን መጠቀም ስለሚኖርበት ካለማቋረጥ ያሰራጨውን ቅስቀሳ ይጠቅሷል። ታዲያ ኢሕአፓ ላይ ከበባው ለዚህ ይሆን? የኢሕአፓን ስም ይዞ እስከማጭበርበር የሚያደርስ? እነ ጌታቸው ኢሕአፓን ለቅቀው መውጣት መብታቸው ቢሆንም አንዳንዶቹ የድርጅቱን ስም ይዘው መንቀሳቀሳቸውን ግን ሁላችንም ልንቃወማቸው ይገባል (“የኢትዮጵያ ሁሉን አቀፍ ሀገራዊ የመግባባት ኮሚቴ” የተሳተፉ ድርጅቶች በሙሉ ኢሕአፓ-አንድነት ብለው ከመካከላቸው የተቀመጡቱ አጭበርባሪዎች መሆናቸው ጠፍቷቸው አይደለም!)። በአብዛኛው የዓለማችን አህጉራት ከሌባ ላይ ዕቃ የገዛ እንደሌባ እንደሚያስጠየቅ ለመሆኑ ያውቃሉ? ይሄ የድርጅት ጉዳይ ነው ብለን ዝም የምንል ከሆነ ግን በሕብረት መሰባሰብ በፍጹም የሚቻል አይሆንም።በመካከላችን ሊኖረን የሚገባ የግንኙነት ሕግጋትና ሥነ-ምግባራት ግልጽ ሊሆኑ ይገባል። ሕብረት ለምንና እንዴት? ዴሞክራሲዊ ሕዝባዊ ሥርዓትን ለመመሥረት ነው። ስለ ዴሞክራሲያዊ አሠራር ደንታ የሌላቸውን ዶ/ሮች በሷቸው ኢንጂኔሮች ወይም የሙቶ አለቆች በያይነቱ የተከበሩ አቶዎች ቢሰበሰቡ በኔ ቤት አፍራሾች ናቸው። ሺህ ዝንብ ቢሰበሰብ መግላሊት አይከፍትም የምለውም ለዚህ ነው። ከበታኞችና ከጸረ ዴሞክራሲ ኢትዮጵያዊነት ከሚጠሉ ኃይሎች ስብስብ ኢትዮጵያዊ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እናመጣለን ማለት ዕብደት ነው (ሕብረት ከማን ጋር ለሚለው መልስ ይሰጣል ማለት ነው)።

**ለማጠቃለል፡-**

በጭቆና ማጥ ውስጥ ያለ ሕዝብ እምቢኝ ብሎ እንደ አንድ ሰው አስቦ ተሰባስቦ ሲያምጽ የሚጨቁነውን ሥርዓት ከሥሩ መንግሎ መጣሉ አይቀሬ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብም አመጽ ያነሳሳው መሠረቱ የፍትሕና የዴሞክራሲያዊ ሕዝባዊ አስተዳደር መጥፋት ነው። ስለሆነም መቆሚያው የወያኔን የክልል ፖለቲካ ከነግሣንግሱና ከነተለጣፊዎቹ መግንሎ ጥሎ በመቃብሩ ሕዝቡ የሥልጣኑ ባለቤት የሚሆንበት፣ ሁሉም ተካባብሮ የሚኖርባትና የሕግ የበላይነት የሚከበርባት አንዲት ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን እውን የምትሆንበት ሁናቴ ማመቻቸት ነው። ይህ አመጽ በነጻ አውጪነት ስም የሚንቀሳቀሱትንም ጠራርጎ የሚያልፍ መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል። ስለሆነም በዚህ ቀውጢ ወቅት ወያኔ እንደ ነበልባል እየለበለበው ያለውን የህዝብ አመፅ ለማዳፈንና እራሱን ለማዳን አይፈነቅለው ድንጋይ መኖሩን አንርሳ! ከመካከላችንም ሁልጊዜ ተሸናፊና ተንበርካኪ ስብስቦችን እያከቸለቸለ የሕዝቡን ድምጽ እያሰማ የትግሉን ውጤት የሚያስበላ መሆኑ የከዚህ በፊቱ ትግል ሊያስተምረን ይገባል። በ97ቱ ምርጫ አካባቢ ሕብረት ሲመሠረት ተሯሩጠው ቅንጅት ብለው የፈጠሩና ሕዝቡን ያማለሉ፣ ያኔ ማንዴላ! ማንዴላ! የተባለላቸው እስከዛሬ የት እንደነበሩና ዛሬስ ምን እያዜሙ እንደሆነ አንርሳ! በጊዜውም ሕብረት ውስጥ የነበሩትም የወያኔ ፓርላማ ዘለው ነው የገቡት። የሕዝቡ ዓመጽ ከፍ ሲል የሕዝብ መፈክር አንስቶ

ጠጋ ጠጋ፤ ሲያመችና የተያዙበት ሉጋም ዘወር ሲያደርጋቸው ደግሞ ገልበጥ ብሎ ካለ ሃፍረት ከወያኔ ሥር መነጠፍ ያየነው የገለማ መንገድ ነው።

ሕዝብ ሠላምንና ዕርቅን የሚያመጣው ፍትሕና ተጠያቂነት ሲኖር ብቻ ነው።ከዚያ ያነሰ አድር ባይነትና እንደ ተለመደው የሕዝብን ትግልና ግለት ለማዶልዶም የሚደረግ እንቅስቃሴ ስለሆነ በዚህ ተራ የተሰለፉትን ማጋለጥ ተግባራችን ይሁን! ስለሆነም በቅርቡ በሶሻል ሚዲያ ያገኘሁት መፈክር ለኔ ተስማምቶኛል

- የወያኔን የጎሣ ካርድ ሁላችንም አቃጥለን ጥለን ኢትዮጵያዊነትን ይዘን ለዴሞክራሲያዊ መልካም አስተዳደር እንዋደቅ!
- ትግሉ ለጥገናዊ ለውጥ ሳይሆን ስር-ነቀል ነው፤ወያኔን ማመን ቀብሮ ነው!

አድርባዮችና ትግል ገዳዮች ይጋለጣሉ!

ኢትዮጵያዊነት ያለጥርጥር በትግላችን ያቸንፋል!

አቶ ሰውየው በሀገሩ ዘብሄረ-ኢትዮጵያ (ከሰሜን አሜሪካ)

1. [የኢትዮጵያ ባለድርሻዎች ጉባኤ የማሕበረ ሰባዊ ድርጅቶች ትብብር]